# ዘመናዊ ትምህርትና ስልጣኔ - 3

……የቀጠለ

የምሁራን ለአገር እድገትና እርምጃ የሚኖራቸውን አስተዋጽኦ ያመከነው የተከሰቱት አምባገነን መንግስታትና ስርአቶች ጭቆናና ተጽእኖ የሚለው የቆየ አመለካከት የተወሰነ ቦታ ቢኖረውም ከላይ እንደተጠቀሰው የአምባገነን መንግስት ቁርቋሪና የስርአቱ የእልፍኝ አስከልካይ ራሱ የተማረው ክፍል በመሆኑ ሚዛን የሚደፋ ምክንያት ካለመሆኑም በላይ አምባገነንነት ከዘመናዊ ትምህርት ጋር የተጣባ /parasite/ ክስተት መሆኑ ምሁሩ ራሱ የችግሩ አካል እንጂ የችግሩ ሰለባ አልፎም የችግሩ መፍትሄ ሊሆን እንደማይችል ነው;;

ዛሬም ተምሬያለሁ የሚለው አካል የስልጣን በትሩን ቢይዝም ባይዝም “ፍለጠው” “ጣለው” “ገርስሰው” የሚሉት ቃላት ከጧት ቡና ጋር ፋት የሚለው የአንደበት ሚሚሻና ውሎ ማሳረጊያው ነው;;

የተፈጠሩትም ስርአቶች ቢሆኑ ባለፈው የሶሻሊሰቱም ሆነ ዛሬ የኤትኒክ ፌዴራሊዝም የታለመውን ከግብ ለማድረስ የሚያስችል ችሎታና ቁርጠኝነት ካለ ለእድገትና ግንባታ የራሳቸው ጠቃሚ ጎኖች /potential/ ያላቸው ነበሩ አላቸውም;; ትናንትና ራሽያን የጠፈር ሳይንስ ባለቤት ያደረጋትና ዛሬ የቻይናን የኢኮኖሚ መዘውር በሙሉ ጉልበቱ የሚያሽከረክረው በዛው በሶሻሊስት ስርአትና ርእዮት ዓለም ያለው አመራር በአንድ ፓርቲ ጥላ ስር ሆኖ ነው;; የእኛ ችግር የሚመነጨው በሚመረጠው መንገድ ወይም በተመረጠው መንገድ ላይ በሚገጥመው መሰናክል ሳይሆን የጀመርነውን የመጨረስ ፣ የታቀደውን ከግብ ለማድረስ ያለን ቁርጠኝነትና መሰናክሎችንም ለማለፍ ያለን ባለሙያነትና የፈጠራ ጠበብትነት ላይ ነው;;

ዘመናዊ ትምህርትን የሚከተለው በሽታ የፈጠራ ስራንና የሚያመክን የምርምር እውቀትንና ችሎታን የሚያደለዱም እንደ ዶ/ር ብርሃኑ አባባል “Lazy and Cynical intellectual Culture” የሚፈጠር፣ አገር በቀል ቅኝ ገዢዎችን የአምባገነንነት ክትባት የሚከትብ ብቻ ሳይሆን የአገር ክህደትን ባህልም የሚያስፋፋ ነው;;

የምሁራን አገርን መክዳትና ለጠላት ማደር የተጀመረው ከመጀመሪያው የኢትዮጵያ ምሁራን ትውልድ /First generation of Ethiopian intellectuals / ጀምሮ እነደሆነ ይታወቃል;; እስከ ጣሊያን ወረራ ድረስ ኢትዮጵያ ያፈራቻቸው ምሁራን /First generation of Ethiopian intellectuals/ ተብለው ከሚታወቁት መሃከል አነዱና እንደ ናሙና /representative/ የሚቆጠረው አፈወርቅ ገ/ኢየሱስ የጦቢያ መጽሔት አዘጋጅ አገሩን ከድቶ ከጣሊያን ወራሪዎች ጋር እነዲያብር ያደረገው ምክንያት ዛሬም ህያውና በሙሉ ሃይሉ ባሁኑ ትውልድ ምሁራን ላይም የመስራት መተቱና ድግምቱ እንደተጠበቀ ነው;;

አፈወርቅ ገ/ኢየሱስ የጣሊያንን ወረራና ኢትዮጵያ በጣሊያን ስር እንድትተዳደር ደጋፊ አባሪ የሆነበት ምክንያትና ጥቂቶቹም እነደ እሱ በግልጽ ባይሆንም በሃሳብ ደረጃ የጣሊያንን በኢትዮጵያ መቆየት /occupation/ እነዲራዘም ይመኙ የነበረበት ምክንያት በወቅቱ የነበረው የፊውዳል ስርአትና ያገሪቱ ባህልና ትራዲሽን ለእድገትና ለለውጥ ፍፁም ፀር የሆነ፣ ይህን የቆየ መሃከለኛ ዘመን /medieval/ ዓለም ውስጥ የሚኖር ህብረተሰብ ጎታች ጉልበት /inertia/ በውስጥ ተራማጅ ሃይሎች ለመግፋትና አንቀሳቅሶ ለመለወጥ እንደማይቻል አምነው ለዚህም የውጭ እጅ አማራጭ የማይገኝለት መፍትሄ እነደሆነ አምነውበት ነበር;;

ይህ ምናልባት በወቅቱ ምሁራኑ ከነበራቸው አነፃራዊ ብዛትም ሆነ ህብረተሰቡን ለመለውጥ ሊያሳድሩት የሚችሉት ተዋፅዖና ተፅዕኖ ውሱንነት የፈጠረው እነደሆነ ተደረጎ ለመረዳት ቢቻልምና የጣሊያን ቅኝ አስተዳደር ሊያስከትላቸው የሚችለው ማህበራዊ አዎነታዊ ለውጦች ሊኖሩ እንደሚችሉ ቢታመንም ቅሉ ዋናው ቁም ነገር ያለውና በጥሞና ሊስተዋል የሚገባው አፈወርቅና መሰሎቹ በጥቅሉ በኢትዮጵያ ህብረተሰብ መሰረቶች ላይ የነበራቸው ጭፍን ጥላቻ /iconoclastic/ አመለካከት ለምዕራቡ ዓለም የነበራቸው ታላቅ ፍቅርና አምልኮ በአንፃሩም በራሳቸውና ባገራቸው ላይ የነበራቸው ዝቅተኛ ስሜት የፈጠረው መሆኑን ነው;;

ትናንት በእነሱ እምነትና ገንዛቤ - ልክ ዛሬም እንደሚታሰበው ማለት ነው - ስልጣኔ ማለት ምዕራባዊነት /westernization/ በመሆኑ መሰልጠንን በኢትዮጵያ እውን ለማድረግ የሰለጠነው የተማረው ክፍል አቅም ደካማ ሆኖ ከተገኘ ዋናውን /original/ አሰልጣኝ ምዕራቡን ቅኝ ገዢ ማምጣት ወይም ከመጣ መቀበል ትክክልና የማይቀር የሃሳብ ቀመር /logical / ድምዳሜ ይሆናል;; ደግሞም የፈረንጅን ስራ ከፈረነጅ የበለጠ ማንም ሊከውነው አይችልምና;;

አፈወርቅም ሆነ ሌሎች ከተነሳሱበት ቅዱስ ዓላማ ጋር ለአገራቸው ያላቸውን ታላቅ ፍቅርና ስሜት ያህል ለምዕራቡ ያላቸው አምልኮና ፍፁም ተገዢነት ምዕራባዊ ላልሆነው ነገር በሙሉ ኢትዮጵያን ልዩ የሚያደርጋትን ማንነትና ምንነት ጨምሮ እነዲጠሉና እነዲያረክሱ አስገደዳቸው;; ከዘመናዊ ትምህርት ጋር የሚገባው /Eurocentric view/ ከምዕራቡ ውጭ ላለው ዓለም የሚኖረው ንቀታዊ ጥላቻ አመለካከት ተጋብቶባቸው ለራስ ማንነት ፣ ለራስ ባህልና ስልጣኔ የዝቅተኝነት መንፈስ አሳድሮባቸው ለጭፍን ጥላቻና ለአገር ክህደት አበቃቸው;;

(እዘህ ላይ ለአገራቸው በሰላሙ ግዜ ለለውጥና ለእድገት በጠላት ወረራም ጊዜ በዲፕሎማሲውም ሆነ በአርበኝነቱ የደከሙትን የትውልዱን ስመ-ጥሮች አለመነሳታቸው ርእሱ ባለመሆኑ ነው;;)

ይህ ባለፈው ትውልድ ያየነው ክህደት አሁን በጊዜያችን ከምናየው የጭፍን ጥላቻ ፖለቲካና አገር ክህደት ጋር ጣምራነት /parallel/ ያለው ብቻ ሳይሆን መነሻ መሰረታቸውም አንድ ምንጭ ነው;;

ዛሬ የኢትዮጵያ ሄሊኮፕተር ወድቆ ቢከሰከስ አንጀቱ ቅቤ የሚጠጣው፣ ባገሩ ላይ ከሚዶልተው ኢሰያስ አፈወርቂ ጋር አብሮ የሚያሴረው ፣ በሽተኛ ወገኑን አልጋ ላይ ጥሎ በተገኘው ቀዳዳ ወደ ውጭ ብርር የሚለው ዶክተር ... ወዘተ ላለው መንግስትና ስርአት ያለውን ተቃውሞና ጥላቻ ሰበብ ያድርግ እንጂ (የኢኮኖሚና የፖለቲካ ስደተኝነት እነዳለ ሳንዘነጋ) የጥላቻው ምነጭ ጥልቅና ከራስ ጥላቻ የሚጀምር ነው;; በመጀመሪያ ደረጃ የሚጠላው ራሱን ነው;; ...የሚጠላው አገሩን ነው;; ....ምክንያቱም ከተማረው ትምህርት ሁሉ ባነደኛ ደረጃ ያገኘው እውቀት ያማረ የረቀቀ የተብረቀረቀ የምዕራብ ህይወት ሃያልነትንና... ባነፃሩ ደገሞ የእርሱንና ያገሩን ኢምንትነት ኮሳሳነትና ዘላለማዊ ጎስቋላነት የሚያሳይ ያንድ ወገን ስዕል ብቻ በመሆኑ ነው;;

በሌላ አነጋገር ዘመናዊ የትምህርት ተቋማት ውስጥ በየደረጃው ስለ ኢትዮጵያ ምንነት፣ ስለ እድገት መሰረቶቿ ፣ ስለ ወቅታዊ ደረጃና የወደፊት ርምጃዎችዋ ፣ ከአካባቢውና ክልሉ ነባራዊና ተግባራዊ አቅጣጫ ጋር የሚያይዝና በፈጠራና በምርምር ተሳትፎን የሚጋብዝ ባንድ ቃል ስለ ኢትዮጵያ ብሩህ የወደፊት ተስፋና እድል የሚያበክርና ለዚህም የሚያዘጋጅ ትምህርት ለማገኘት

ባለመታደሉም ጭምር ነው;;

የተማረው ከተማረ ከሰለጠነ በሁዋላ ፈረነጅነት ይሰማዋል...ሁሉን ነገር በፈረነጆች ዓይን ማየት ይጀምራል .... የሚያይው ሁሉ ያስጠላዋል... አገሩ ያስጠላዋል ...ድሃው ህዝብ ይደብረዋል ...ኑሮው ይቀፈዋል;; በተለይ ፈረንጅ አገር ከገባ በኋላ በፊት አገሩ እያለ የማያስጠላው ነገር በሙሉ ያስጠላዋል ... ያገሪቱ መሪዎች እኩይነት ... የፖለቲካው አስቀያሚነት ... ሁሉም ነገር ጠቁሮ ጨልሞ ከብዶ ይታየዋል ... እነጭጭ ዲሞክራሲው ያበሸቀዋል ...ያስቆጣዋል;; ፖለቲካውም ውስጥ ከገባ ዘራፍ ይቀናዋል ... ምናባቱንስና አታወረዱትም እንዴ ...አውርዱት ! ይላል በቁጣና በንዴት ;;

ትናንትን በዛሬ የግዜ ተራራ ላይ ቆሞ ቁልቁል ወደታች እያዩ መፍረድ ባይቻልም የዛሬን በሽታ ለማገምና ለማገገም የበሽታውን ታሪክ ማወቅና መረዳት የመጀመሪያው ፈውስ በመሆኑ ወደሁዋላ አዝሮ ማየት ግዴታ ነው;;

ሁለተኛው የኢትዮጵያ የምሁራን ትውልድ / second generation of Ethiopian intellectuals/ የሚባለው ከጣልያን ወረራ በሁዋላ የተከተለው ሲሆን አፈወርቅን ለክህደት የዳረገው በሽታ አሁን ባለንበት ጊዜ እነደምናየው ቅርፁን ቀይሮ የብሄር ብሄረሰቦችን የመብትና የእኩልነት እውነተኛ /genuine/ የዲሞክራሲያዊ ጥያቄዎች ላይ ተጣብቶ /parasite/ አድርጎ ይገኛል;;

ይቀጥላል

ጃዊሳ